የፍትህ ተቋማት ህገ መንግስታዊ መብቶችን በመጠበቅ ረገድ ያሳቸው ድርሻ

አዘጋጅ

አቶ ውብሸት ሽፈራው

የፍትህ ተቋማት ህገ መንግስታዊ መብቶችን በመጠበቅ ረገድ ያላቸው ድርሻ

መግቢያ

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በ1945 ዓ.ም ሲመሰረት በቻርተሩ ውስጥ ከተቀመጡት አላማዎቹ ውስጥ አንዱ ለሁሉም ስዎች የሚገቡ ሰብአዊ መብቶችና መሰረታዊ ነፃነቶችን ማስፋፋትን እና ማስከበርን ማበረታታት ነው። በዚህ መሠረትም የ1948 ዓ.ም የሰብአዊ መብቶች መግለጫ ሰነድ፣ የሲቪል፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ አለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ ሰነዶች እየፀደቁ ወጥተዋል። አገራችንም በተለያየ ጊዜ የወጡትን ዋና ዋና የሰብአዊ መብት ሰነዶችን በተለያየ ጊዜ አፅድቃለች፣ ተቀብላለች የራሷም አድርጋለች። ይህ መሆኑ አገራችን ሰብአዊ መብትን አስመልክቶ ያላት የእውቅናና የጥበቃ ደረጃ አለም አቀፍ ደረጃን እንዲይዝ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ለመብቶቹ መፈፀምም (መተግበርም) አይነተኛ መነሻ መሳሪያ ነው። በሌላ በኩል መብቶችን በተመለከተ በሰነዶች ላይ የተቀመጠውን አባላት ህግ የማውጣት ወይም ሌላ ለተገበር አመቺ የሆነ ርምጃ የመውሰድ ግዴታን መወጣት ነው። የሰብአዊ መብት ሰነዶችን ተቀብሎ ከማፅደቅ በተጨማሪም አገራችን ለአፈፃፀሙ አመቺ እንዲሆን የተለያዩ እርምጃዎችን ወስዳለች። ዝርዝር የሆነ የሰብአዊ እና የነፃነት መብቶች የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክሪሲያዊ ሪፐብሊክ (ከዚህ በኃላ ህገ መንግስቱ) ህገ መንግስት አካል እንደሆኑ ተደርጓል። የህገ መንግስት ድንጋጌ ትርጉም በሚያስፈልገው ጊዜም አገራችን ከተቀበለቻቸው የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ህግጋት እና ስምምነቶች ጋር ብቻ ሳይሆን ከመርሆዎች ጋርም በተጣጣመ መንገድ መተርጉም እንደሚገባው ህገ መንግስቱ ደንግጓል። በህገ መንግስቱ መሰረታዊ የሆኑት የሰብአዊ እና የነፃነት መብቶች የተደነገጉት ሁሉን አቀፍ (Comprehensive) በሆነ መልኩ ነው። የሲቪል ፣ ፖለቲካል ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና የቡድን መብቶችን ባካተተ መልኩ የተደነገጉ ሲሆን ሲሻሻሉ፣ ለገደቡ የሚችሉትም እጅግ ልዩ በሆነ የህገ መንግስቱ ስርዓት ብቻ ነው።

ይህም በመብቶቹ መሀል በመሰረቱ መበላለጥ ሳይኖር ለመብቶችም ትግበራ የዳኝነት (Judicial Supremacy) (አሜሪካ) ወይም የፓርላማ (Parliamentary supremacy) (የእንግሊዝ) የበላይነት ሳይኖር በህገ መንግስት የበላይነት (Constitutional Supremacy) መርህ ላይ ብቻ እንዲፈፀም የሚያስችል አበይ መንገድ ነው።

የመብቶችን አመዳደብ እና ምክንያቱን በተመለከተ አገሮች የየራሳቸውን ምርጫ ሊከተሉ ይችላሉ። ዝርዝሩ በሌላ ክፍል ይሸፈናል። እንዳንድ አገሮች መብቶቹን በሙሉ በአንድ ምዕራፍ ስር ሲያስቀምጡ ሌሎች ደግሞ በበርካታ የህገ መንግስት ምዕራፎች ስር ያስቀምጣሉ። አገራችንን በተመለከተ በህገ መነግስቱ መግቢያ ላይ እንደተመለከተው የነበረውን ታሪካዊ ስህተት በማረም ፣በመግባባት እና በመቻቻል ላይ የተመሰረተች አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ያላትን አገር ለመመስረት ሰብአዊ መብትን አስመልክቶ የወሰደቺው አማሪጭ ሁሉንም **"መሰረታዊ"** በማድረግ ነው። መብቶቹ ሁሉ **"መሰረታዊ"** ሆነው ሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ ተብለው ተመድበዋል።

ይህም መብቶቹ አለም አቀፋዊ፣ የማይከፋፈሉ፣ የተያያዙና የማይነጣጠሉ መሆናቸውን አያሰቀረውም። እነዚህ መብቶች በህገ መንግስቱ ከአንቀፅ 13 እስከ 45(1) ድረስ የተመለከቱት ሲሆን በዚህ ክፍል ውስጥ በዝርዝር የምንመለከታቸው አይደሉም፡ በዚህ ክፍል ውስጥ በዝርዝር የምንመለከተው የቡድንና የግለሰብ መብቶችን አፈፃፀም አስመልክቶ የፍትህ አካላት የላቸውን ሚና ብቻ ነው።

1. የቡድን መብቶች (Collective Rights)

የቡድን መብቶች የምንላቸው ሰዎች በማንነታቸው ወይም በተለየ የጋራ ፍላጐታቸው የተነሳ በሌላ አካል ከሚደርስባቸው ጥቃት ለመከላከል የሚያስችሉአቸው የተወሰነ ስብስብ (Group, collection) ማንነት መስጠበቂያ መብት ነው። በቡድኑ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ግለሰባዊ መብት ድምር ሳይሆን ቡድኑ እንደ ቡድን ይገቡኛል፣ ይጠበቁልኝ የሚላቸውን መብቶች የሚያካትት ነው። የሰብአዊ መብቶች በታሪካቸው ለመጀመሪያ ጊዜ እውቅና አገኙ

ከሚባሉበት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ6ኛው አመተ አለም አንስቶ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የቡድን መብቶች እውቅና ሳያገኙ ቆይቶዋል። የሰብአዊ መብት የቀደሙ ታሪኮች የሚያነሱት የመብቶች ጥያቄ ግለሰብን መሰረት ያደረገ የተፈጥሮ ስነ ህይወት (Biological theory) ኃይማኖትን (Natural Theory) እና ፍላጐትን (Interest theory) ስለነበር የቡድን መብት እውቅና አልማግኘቱ የሚደነቅ አይደም። ይህ ማለት ግን ሰዎች ከጥንት አንስቶ በቡድን የመኖር ልምድ አልነበራቸውም ማለት አይደለም። አፍሪካ በተለይም ደግሞ የአገራችን የረዥም ጊዜ ታሪክ የሚያሳየን የህብረተሰብ አኗኗር በመሰረቱ ቡድናዊ መሆኑንና የቡድን ፍላጐት ብቻ ሳይሆን የግለሰብ ግዴታን ጭምር በቡድን ለመፈፀም ፍላጐት የነበረ መሆኑን ነው። ለዚህም ይመስላል አንዳንድ ተችዎች ሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች መሠረት አንድን የአለም ክፍል ያገላል፤ መሠረታቸውም "ሞራል" እና "ሰው" አዊ ምክንያቶች ቢሆንም ተጨባጭ የሞራል መሰረት (Objective, reasoned moral) ያጣሉ የሚሉት።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ ባለፉት 30 አመታት ውስጥ የቡድን መብት ይጠበቅልን "ጩኸት" አዘል ጥያቄ በአለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ጥያቄ እየሆነ መጥቷል። በተለይ ከሶቭየት ህበረት መፍረስ፣ ከቀድሞው የጐዝላቪያ እና ከደቡብ አፍሪካ ማህበራዊ ለውጥ በኃላ ጥያቄው እየጐላ መጥቷል። ይህ በአብነት በግልፅ የሚታወቀውን ለመግለፅ ያህል እንጂ በአለም ላይ በአሁኑ ሰዓት ከሚገኙት አገሮች ውስጥ በርካቶች የ30 አመት እና በታች እድሜ ያላቸው ተመሳሳይ ጥያቄ የሚያነሱ ናቸው። በርካቶቹ ከኮሎኒያሊዝም ውጤት በማገገም ላይ ያሉ ወይም ማገገም ያልቻሉ ነገር ግን የኢኮኖሚ እና ፖለቲካዊ ነፃነታቸውን (Independence and identity) ማረጋገጥ የሚፈልጉ ናቸው። በዚህም የተነሳ በአለም ላይ ያሉ ቡድኖች በተለይ በባህል፣ በሐይማኖት እና በቋንቋ ረገድ ያላቸውን ልዩነት በይፋ ለመግለፅ የሚያስችላቸውን መብት በመጠየቅ ላይ ናቸው። የአብዛኛውን ቡድን (ለምሳሌ በዘር) በጭቆና ስር የቆየውን ስርዓት እና ተቋም ለማስወገድ በመፈለግ ብቻ የመጣ አይደለም። ፍላጐቱ የአንድ ዘር፣ ቡድን ጥቅም ብቻ የተመሰረተም ሳይሆን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስብሰባዎች ላይም ብሔራዊ (አገራዊ) ፍላጐት ሆኖም

የሚቀርብ ነው። የፍላጐት መነሻ ምክንያቶች በርካታ ናቸው። የሰው ልጅ አፈጣጠር በልዩነት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ይህ ልዩነት ሳይጨፈለቅ ተከብሮ መኖሩ ለአለም (ብሎም ለአገር) ሰላምና ልማት መሰረት ነው። በሰለጠነው አለም ልዩነትን መጨፍለቅ ውጤቱ ውድመት ነው የሚሆነው። የማንነት ጥያቄ አለመመለሱ ለእድገትና ለብልፅግና መሠረት የሚሆኑ ፈጠራዎች (doom to creativity) እንዲከስሙ የሚያደርግ ነው። አሁን ባለንበት ዘመን የተሻለው የህዝብ አስተዳደር ዲሞክራሲያዊ የህዝብ አስተዳደር መሆኑ ጥያቄ ውስጥ አይገባም። አገራችንም ይህንን የህዝብ አስተዳደር መርህ እየተገበረች ነው። መሰረታዊ የዲሞክራሲያዊ የህዝብ አስተዳደር መርህ ምሳሌዎች ከሚባሉት ውስጥ የአነስተኛው (ቡድን፣ ዘር...) መብት መከበር፣ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ብዙህነትን (Plularism) መቀበል፣ መተግበር እና መቻቻል (መረዳዳት) ይገኝበታል። ይህም ቡድንና መሰረት ያደረጉ ለዩነቶችን ማስወገድ እንደማይቻል ብቻ ሳይሆን ቡድኖች ምርጫቸውን ሆነ መጨረሻቸውንም የመምረጥና የመወሰን መብት ሊኖራቸው እንደሚገባ ያሳያል። የቡድን (ዘር፣ ህዝብ) ራሱን እንደገለፀ እና ፍላጐቱን እንዲተገብር ማድረግ የነፃነት ጥያቄ ቁልፍ ጉዳይ ነው። ለዚህም ነው ፀሐፊዎች "…. The ability of people to define themselves and to exercise their will is the very essence of liberty" በማለት የሚገልፁት። ይህ እስካልሆነ ድረስ ከባርነት ነፃ ቢወጣም እውነተኛ ነፃነት (true Freedom) ተገኝቷል ለማለት ግን አይቻልም።

በአንድ አገር ውስጥ በእርግጥ እውነተኛ ሰላም እና ፍትህ ሰፍኗል ለማለት አንደኛው በሐር፣ ዘር ወይም ሌላ ቡድን ይነስም ይብዛም የሌላኛውን ማንነት፣ ፍላጐት፣ ምርጫ እና መጨረሻ መጨፍለቀ (በመዋጥ) የለበትም። ይህ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም የሁለቱ ቡድኖች ፍላጐት እንዴት ሊጣጣም ይችላል? በቡድን ውስጥ ያለ የግለሰብ መብት ከቡድኑ መብት (ፍላጐት) ጋር እንዴት ሊጣጣም ይችላል ? የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። ይህንን ለመመለስ ደግሞ በሚከተለው መልኩ ሚዛን መስረት ያስፈልጋል።

1. አንድ ብሐር፣ ዘር ወይም ቡድን የቀረውን ሌላ ቡድን እንደ አንድ ራሱን የቻለ ቡድን መመልከትና መቀበል ይኖርበታል። ትልቁም

ይሁን ትንሹም ቡድን ያሉትንና የራሱ መለያ የሆኑትን ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ ባህል፣ የፍትህ ስርዓት፣ ወዘተ በሌላ ሳይዋጡበት የማንነቱ እና የህልውናው መገለጫ በመሆን እንዲኖርበት እንደሚፈልገው ሁሉ ሌላውም ቡድን እኩል እና ተመሳሳይ ፍላጐት ያለው መሆኑን መረዳትና መቀበል ይኖርበታል። ፀሐፊዎች “Mutual Recognition” ይሉታል።

2. በሌላ በኩል ቡድኑ በራሱ የግሉ የሆነ በርካታ መለያዎች እንዳሉት ሁሉ ከሌላው ጋር የሚያመሳስለው፣ የሚያቆራኘው እና የማይለየው መብትም ይኖሩታል። አገር Multi-cultural እንደሆነውም ሁሉ Inter —cultural ነው። ስለሆነም የራስን ማንነት ጠብቆ የመኖር ፍላጐት የመኖሩን ያህል የጋራ ማንነትንም ጠብቆ አብሮ ለመኖር ፍላጐት ይኖራል። እነዚህን ሁለት ፍላጐቶች በማጣጣም አብሮ ለመዝለቀ የጋራ ስምምነት ያስፈልጋል። ፀሐፍት “ Mutual consent” ይሉታል።
3. አብሮ የመቆየት ስምምነት ቀጣይነት ያለው ሊሆንም ይገባል። እውቅና መስጠት (መቀበል) እና የስራቱ በዚሁ መሰረት አብሮ የመኖር ፍላጐት የስርዓቱ መጀመሪያ ብቻ ሳይሆን ማስቀጠያና የጋራ ግብ ማሳኪያ ሊሆንም ይገባል። ይህንን ፀሐፊዎች “Mutual Continuity” ይሉታል።

እነዚህን 3ቱ ቀመሮች የያዘ የቡድን ስብስባ (አገር) ዘላቂ ሰላም በሰፈነበት መልኩ በአንድነት የሚኖር ሊስማማና ሊበለፅግ የሚችል እንደሆነ ፀሐፊዎች ይስማሙበታል።

ወደ አገራችን ህገ መንግስት ስንመለስ ከፍ ሲል የተገለፁትን መሠረት ሃሳቦች በህገ መንግስቱ ለተለያዩ ክፍል ውስጥ ተክተው እናገኛቸዋለን። በመሠረቱ ህገ መንግስቱ የፀደቀው የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መከረውበት ባሳለፉት ውሳኔ መሰረት ነው። "ብሔር

ብሔረሰቦች እና ህዝቦች" ሰዎች በአንድነት የፈጠሩት ማህበረሰብ (a group of people) ነው። ይህ ማህበረሰብ የጋራ የሆነ ባህል ፣ ቋንቋ፣ ተመሳሳይ ልምድ፣ ህልውና ያለው ሆኖ አንድ የሆነ ስነ ልቦና ያለው ነው። ህገ መንግስቱን ያፀደቁት በዚህ መልኩ በተለያየ ስነ ልቦና የሚኖሩ የማህበረሰብ ስብስብ ናቸው። ህገ መንግስቱን ሲያፀድቀው የአንድ ባህል ወይም ኃይማኖት ከሌላው ባህልና ኃይማኖት የሚበልጥ መሆኑን በመገንዘብ ሳይሆን ሁሉም የተለያዩ ባህሎችና ኃይማኖቶች "ካለ አንዳች ልዩነት እንዲራመዱ" ለማድረግ በፅኑ በማመን ነው። ከፍ ሲል በተመለከተው አይነት አንዱ ብሔር ብሔረሰብ እና ህዝብ ለራሱ ባህል፣ ወግ፣ ኃይማኖት የሰጠውን ክብደት ያህል ለሌላውም ሰጥቷል። ይህም የአንድ ኃይማኖት ጠባቂ ወይም ከአንድ ስርወ መንግስት የመጣ ሰው ብቻ ህገ አውጪ፣ ህግ አስፈፃሚ እና የመጨረሻ ዳኛ ሆኖ በቆየበት አገር ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ ነው። ህገ መንግስት እኔ አበልጣለሁ የሚል ሳይሆን "እኩል ነን፣ እኩል እንራመዳለን" የሚል ስርዓት እና ተቋም ለመፍጠር የተቆጠረበት ነው። ብሔር ብሔረሰብ እና ህዝቦች ይህንን ሲወስኑ በራሳቸው "ነፃ ፈቃድ" ፣ "ፍላጐት"፣ "እምነት" ላይ ተመስርተው የየራሳቸው አኩሪ ባህል እንዳላቸው፣ ሁሉም የጋራ ጥቅምና አመለካከት ያላቸው መሆኑንም በመገንዘብ ነው። በዚህ በኩል የመጣው ህገ መንግስት ለዘላቂ ሰላም ዋስትና፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገትን የሚያፋጥን፣ የተዛቡ ታሪካዊ ግንኙነትን የሚያርም፣ የጋራ መብትና ጥቅምን በማስከበር አንድ የጋራ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚያስችል እንደሆነም ያምናሉ። ይህንን ለማሳካት በዝርዝር ከተመለከትን ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱን እንከን መለወጥ (ማሻሻል) ቢያስፈልግ በተመሳሳይ ፈቃድ ላይ ተመስርቶ መሆን እንዳለበትም አስምረውበታል። ይህም ቡድኑ ለመኖር በአንድ ቅርጫት ውስጥ መጠቅለል ያለበት ሳይሆን (policy of assimilation) (Mutual Recognition, consent እና Mutual continuity) በጥንቃቄ ተመዝኖ መቀመጡን ያስረዳናል።

የህግ አውጪው ፣ የህግ አስፈፃሚው፣ የህግ ተርጓሚው፣ የኃይማኖት እና ባህላዊው ተቋም፣ የህግ ትምህርት ቤቶችም እንዲሁም ሌሎች የፍትህ አካላት በሙሉ ተግባራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ሁሉ ይህንን የማህበረሰቦች ቡድኖች ፍላጐት መነሻና መድረሻ ግምት ውስጥ ማስገባት ህገ መንግስታዊ ግዴታ ሆኖ ይጠበቅባቸዋል፡፡ አንዱ ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ህዝብ ከ3ስቱ አንዱ ጐድሎብኛል በማለት ጥያቄ ቢያነሳ ጥያቄውን ተቀብሎ የሚያስተናግደው የፍትህ አካላት ፀሐፊዎች እንደሚሉት ጥያቄው “መልካም” እና “በፍትህ የሚመለስ” መሆኑን ተረድተው በህጉ መሠረት አግባብ ያለው “የውጪ ጥበቃ” “External protection” ሊሰጡት ይገባል፡፡

የግለሰብ መብቶች

የግለሰብ መብቶች የምንላቸው ሰዎች ግለሰብ በመሆናቸው ብቻ የሚኖራቸው መብቶች ናቸው፡፡ የግለሰቦች መብቶች አንድ ሰው በማህበረሰቡ ውስጥ አገልግሎት ክፍፍልን አስመልክቶ ከሌላ ሰው ጋር ያለውን ግንኙነት የሚመራበትን መርህ የያዘ ነው፡፡ የጋራ ጥቅም በመያዛቸው ወይም የሞራል ጥያቄ መሠረት ስላላቸው ወይም በውል ህግ በመታሰራቸው ወዘተ የተነሳ የከበራሉ (የታወቃሉ)፡፡ አንድን ድርጊት ለመፈፀም የሚያስችሉ (Claims to freedom of action) በመሆናቸውና መንግስት ከመመስረቱ በፊት የነበሩ በመሆናቸው ሰብአዊ መብቶች እና ሲቪል መብቶች ከምንላቸው ጋር ሙሉ በሙሉ ላይገጥሙ ይችላሉ፡፡ የእነዚህ መብቶች ክፋይ (አካል) ግን ናቸው፡፡ የግለሰብ መብቶችን አስመልክቶ የፍትህ አካላት በጥቅሉ ከፍተኛ ወገን ጠባቂነት፣ አጣሪነት እና አሳሳቢነት ሚናቸውን በአግባቡ ሊወጡ ይገባል፡፡

የቡድንና የግለሰብ መብቶችን በመጠበቅ ረገድ የፍትህ አካላት ሚና

ከፍ ሲል የተመለከትነው የግለሰብ እና የቡድን መብቶችን ምንነት እና መሠረታቸውን ነው፡፡ በሌላ ፅሁፍ በዝርዝር ሊታዩ የሚችሉ በመሆናቸው በአጭሩ ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ ቀጥለን የምንመለከተው እነዚህን መብቶች በመጠበቅ (በማስከበር) ረገድ የፍትህ አካላት ሚና ምን ሊሆን ይገባል የሚለውን ነው፡፡

ከቅርብ አስርት አመታት ወዲህ እየመጡ ያሉ ህገ መንግስታት የሚይዟቸው አንድ አገር ወይም ህዝብ ሊኖረውና ሊደርስበት የሚፈልገውን ግብ ምኞት (Aspiration) ብቻ ሳይሆን በቀጥታ በፍትህ አካላት ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚገባቸውን ድንጋጌዎችንም ጭምር ነው፡፡ የአገራችን ህገ መንግስት በዚሁ መስመር የሚገኝ ነው፡፡ ለዚህም ነው ህገ መንግስት በአንቀፅ 9(2) ላይ ህገ መንግስት በራሱ ሊከበር የሚችልና ገዥ እንደሆነ የደነገገው፡፡ እንደቀድሞው ጊዜ ሁሉ ህገ መንግስቱን ለማስከበር፣ ለማክበር እና በዚሁም መሰረት ለመገዛት ሁል ጊዜ ተጨማሪ አዋጅ፣ ድንጋጌ አያስፈልገውም፡፡ ማንኛውም የፍትህ አካላ መንገዶቹ ቢለያዩም ህገ መንግስቱን የማስከበር እና በህገ መንግስቱ የመገዛት ግዴታ ያለበት መሆኑን መገንዘብ ይኖርበታል፡፡ ይህን ለመፈፀም ደግሞ ህገ መንግስቱን ስራ ላይ ማዋል (Apply) እና በአግባቡ መፈፀም (Enforcement) ይገባል፡፡ የፍትህ አካሉ ህገ መንግስቱን የማስከበር ኃላፊነት (ግዴታ) ያለበት በመሆኑ ይህን ሊያደናቅፍ ለሚችል ህግ፣ ውሳኔ ፣ ልማዳዊ አሰራር ዋጋ መስጠት አይገባቸውም፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ ህጉ ውሳኔው ወይም ልማዳዊው አሰራር ህገ መንግስቱን ከመውጣቱ በፊት ወይም በኃላ (pre or post constitution) የወጣ (የነበረ) መሆኑ ለአገራችን ለውጥ አያመጣም፡፡ ሰለሆነም በህገ መንግስቱ ውስጥ የተመለከቱትን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግቦች ተጨባጭ እና ትርጉም ባለው ሁኔታ ተፈፃሚ ከማድረግ ባሻገር ህገ መንግስታዊ ተልዕኮን ለመፈፀም በሚያስችል መልካም መጠገን (mounding) ይጠበቅባቸዋል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ህጐች ሁሉንም ጥያቄ ላይመልሱልን ይችላሉ፡፡ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ሰርዓት ህጉ በራሱ በርካታ ክፍተቶች ያሉበት በመሆኑ አለዚያም ደግሞ ከህገ መንግስቱ ጋር የማይጣጣሙ ድንጋጌዎችን በመያዙ የአፈፃፀም ክፍተት ሊፈጠር

ይችላል። በዚህ ጊዜ የተፈጠረን ክፍተት በህገ መንግስቱ ቀጥታ ድንጋጌዎች ይህ ባይቻል ደግሞ በህገ መንግስቱ መንፈስ መሰረት መሞላት ይኖርባቸዋል። የሰብአዊ መብቶችን አስመልክቶ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህጉ ተመሳሳይ ችግር ባለበት የፍትህ አካሉ የህገ መንግስቱን መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ድንጋጌ በጥንቃቄ ተግባሪዊ በማድረግ ክፍተቱን መሙላት ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ረገድ በተለይ የዳኝነት አካሉና የዐ/ህግ ባለሙያዎች ተግባራቸው ሁሉ መነሻ እና መድረሻው እነዚህን ድንጋጌዎች መሆናቸውን በስራቸው በውሳኔያቸው በትዕዛዛቸው በአሰራራቸው የማያመለክቱበት ምክንያት ሰልጣኖች ሊወያይበት ይገባል።

በሰብአዊ መብቶች ዙሪያ ያሉ ክፍተቶችንና ግጭቶችን የሚፈቱልን ህገ መንግስቱ የአገሪቱ ህግ አካል የደነገጋቸው አለም አቀፍ ስምምነቶችም ጭምር ናቸው። ኢትዮጲያ ያፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች በደረጃቸው ከህገ መንግስቱ በታች ሆነው የአገሪቱ ህግ አካል ናቸው። በአገሪቱ ውስጥ ሊከበር ስለሚገባው መሰረታዊ የሰብአዊ መበት እና ነፃነት መሰረትም (ምንጭ) ናቸው። ስለሆነም የፍትህ አካላት የህገ መንግስቱን ሰበአዊ መብት ድንጋጌዎች በመተርጉም መፈፀም ቢያስፈልጋቸው እነዚህን አለም አቀፍ ድንጋጌዎችና መርሆዎች መመርመር አለባቸው። በሌላ በኩልም አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶችን (እስካፀደቁ ድረስ) ተርጉመው መፈፀም ይችላሉ። አለዚያም ደግሞ በቀጥታ ተፈፃሚ ማድረግ ይችላሉ። በዚህ ረገድ በተለይ በዳኝነት እና በዐቃቤያነ ህግነት ስራ ላይ የተሰማሩ የህግ ባለሙያዎቻችን ስምምነቶችን ከውስጥ ጉዳዮች ውጭ ለመተግበር አለመጣራቸውና "ፈጠራ" (Create judge, creative public prosecutor) ለመሆን አለመሞከራቸው ለውይይት ክፍት ነው።

ስለሆነም በህገ መንግስቱ ውስጥ የተካተቱትን መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች አስመልክቶ የፍትህ አካላት፤

1. መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች አለም አቀፋዊ መሆናቸውና በህገ መንግስታችን ውስጥ ተካተው ጥብቅ የሆነ የፍትህ አካላትን ትኩረት የሚሹ መሆናቸውን፤
2. በተለይ ነፃ ገልልተኛ እና በአግባቡ የስለጠነ (የበቃ) ባለሙያ ያለው የዳኝነት ስርዓቱ መብቶችን በማስከበር ረገድ የተለየ ቁልፍ ሚና ያለው መሆኑንና

በእያንዳንዱ ውሳኔውና ተግባሩ ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌና መንፈሱ በህብረተሰባችን ህይወት ውስጥ እውን የሚሆን መሆኑን፣

3. የኢኮኖሚ፣ ሶሻል፣ ባህላዊ እና የቡድን መብቶች ለማስፈፀም ከዳኝነት አካሉ ይልቅ የሌሎች አስፈፃሚ አካላት ሚና ቀዳሚ ቢሆኑም ለዳኝነት አካሉ ተግባርም ወሳኝ የሆነ ማጣቀሻዎች (Vital Points of reference) እንደሆኑ፣
4. ሰብአዊ መብት ጉዳዮች በፍጥነት የሚታዩ፣ ጥሰቶችም በአግባቡ የሚካሱ መሆን እንዳለባቸው፣
5. በዚህ ረገድም የሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ የእንባ ጠባቂ ተቋም ጥሰቶችን የመመርመር፣ የመቆጣጠር፣ የምርምር እና ትምህርት ተግባራትን በስፋት መወጣት ያለባቸው መሆኑን፣
6. የፍትህ አካላት በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ የዳኝነት አካሉ በህግ የሰለጠነ ብቻ ሳይሆን ህዘቡ በሰብአዊ መብቶች ዙሪያ ያለውን ሰሚት፣ ፍላጐትና ምኞት በአግባቡ የሚረዳና ምላሽ የሚሰጥ መሆን እንዳለበት፤ በተለይ ደግሞ ለጉዳት ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍላጐትና ችግር የሚረዳና በዚህ የተነሳም ለሰብአዊ (ቡድን) መብታቸው ልዩ ትኩረት የሚሰጥ የፍትህ አካል የሚያስፈልግ መሆኑን፣
7. የሰበአዊ መብት የሚመለከቱ ጉዳዮችን በተመለከተ የፍትህ አካሉ አቢቱታዎችን የሚቀበልበትን እድል ማስፋት እና በተለየ መልኩ የበለጠ ተደራሽ የሚሆንበትን መንገድ መሻት ያለበት መሆኑን፣ ፍትህን ለተከሳሽ ብቻ ሳይሆን ለተጐጂውና ለህብረሰተቡ በአጠቃላይ ማድረስ ያለበት መሆኑን የሚገነዘብ የፍትህ አካል መሆን ይኖርበታል።

የግለሰብ መብቶችን በማስፈፀም ረገድ

በአንድ ወቅት የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአንድ አገር ስልጣኔ ከሚለካባቸው መንገዶች ውስጥ የወንጀል ህግ በአገሪቱ ውስጥ የሚፈፀምበት መንገድ መስፋቱ ወይም መጥበቡ ሰፊ ቦታ እንደሚሰጠው ገልፆል። የዚህን እንድምታ በመገንዘብ የመሰለ ህገ መንግስቱ በምዕራፍ ሦስት ስር ሰፊ የሆነ የወንጀል (ስነ ስርዓት) ህግ ድንጋጌዎችን የያዘው። የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎችና መንፈስ ሰፋ አድርገን

ከተመለከትናቸው በወንጀል ክርክር ሂደት ውስጥ ከመነሻ እስከ መጨረሻው ባለው ሂደት ላይ ወሳኝ የሆነ ተፅዕኖ ያላቸው ናቸው፡፡ በስነ ስርዓት ህጉ ውስጥ የወጡ ዝርዝር ህጐችም ከዚሁ ጋር በተጣጠመ መልኩ ሊተገበሩ የሚገባቸው ዝርዝር ማስፈፀሚያዎች ናቸው፡፡ ሁሉም የፍትህ አካል በሁሉም ሂደት ውስጥ ያላቸው ሚና እና ተሳትፎ ደረጃው ይለያል እንጂ ዜሮ የሚባል አይደለም፡፡ ይህ ማለት አንዱ የፍትህ አካል በሌላኛው የፍትህ አካል ውስጥ በመሰለው እየገባ የሙያ እና ተቋማዊ ነፃነትን ሊጋፋ ይችላል ለማለት አይደለም፡፡ ስራዎች በነፃነት ይሰሩ ይገባል ማለት ግን ከህገ መንግስቱ ድንጋጌ እና መንፈስ ውጪ ይሰራል ለማለት አይደለም፡፡ ተግባሮች ከህገ መንግስቱ ውጪ ተፈፅመው የህግ የበላይነት እንዳይጠፉ ግን በዝርዝር ህጐች መሠረት የቅደም ተግባር እና የድህረ ተግባር ቁጥጥር እና ተጠያቂነት ይኖራል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ የፖሊስ አባል የተፈፀመን ወንጀል መነሻ በማድረግ የምርመራ ሰራ በሚያከናውንበት ጊዜ ስለሚያዙ ንበረቶች እና ሰዎች፤ ስለሚበረበሩ ንበረቶች በፍርድ ቤት መመሪያ ሊሰጠው ይችላል፡፡ የፖሊስ አባሉ የሚፈፅመው የምርመራ ተግባር እና ፍርድ ቤት የሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረቱ የህገ መንግስቱ (ምሳሌ አንቀፅ 17(1)) ድንጋጌ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም የፖሊስ አባል የፈፀመው ምርመራ ካለዚህ መነሻነት ከተሰጠው መመሪያ ውጪ ከሆነ በሌላ የፍትህ አካል ይጠየቃል፡፡ በተመሳሳይ መልኩም ፍርድ ቤት የሰጠው መመሪያ ከህገ መንግስቱ መንፈስ ውጪና ከስነ ስርዓት ህጉ ድንጋጌዎች ውጪ ከሆነ አሁንም በሌላ አካል ይጠየቃለ ማለት ነው፡፡ የምርመራው ተግባር ከተፈፀመ በኃላ መዝገቡን የሚረከበው ዐ/ሕግ በህጉ መሰረት ሊፈፅማቸው የሚገቡ 5 አማራጮች አሉት፡፡ ይህንን አማራጭ ዐ/ሕግ በአግባቡ ሊጠቀምበትና በሰብአዊ መብት ጥሰት ቢደርስ ለምሳሌ የዳኝነት አካሉ ምን መፈፀም ይገባዋል የሚለውም ተመሳሳይ ጥያቄ ነው፡፡ አንዳንድ ፀሐፊዎች በአገራችን ህግ መሰረት ፍርድ ቤት በዚህ ደረጃ ጣልቃ ገብቶ ስህተት የሚያስተካክልበት ህግ የለም ይላሉ፡፡ ዝርዝሩ በስነ ስርዓት ህገ ውስጥ የሚታይ ቢሆንም ፍርድ ቤት በህገ መንግስቱ ውስጥ የተመለከቱትን የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች የማስከበር ግዴታው በዚህ ደረጃ የለም ለማለት ይቻላል ስልጣኞች ይወያዩበት፡፡

ሰብአዊ መብቶች ጥበቃ የሚሹት በምርመራ እና ከምርመራ በኃላ ክስ በፊት ባለው ጊዜ ብቻ ሳይሆን ክሱ በሚሰማበት ጊዜም ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ከፍትህ አካላት

በይበልጥ የዳኝነት አካሉ ሚና ወሳኝ ነው። የቀጠሮ ቀን ከመወሰን አንስቶ ፍርድ እስኪሰጥበት ጊዜ ድረስ ያለውን ሂደት የሚቆጣጠረው ፍርድ ቤቱ ነው። በሂደቱ ውስጥ የግለሰብ መብትን መጣስ የሚያስከትሉ በርካታ ጥያቄዎችን ሊነሱ ይችላሉ። ጥያቄዎቹ ተካራካራው የሆነው ግለሰብ የገንዘብ እና የእውቀት ካፒታል የሌለው ከመሆን የሚነሱ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ የዳኝነት አካሉ የሰብአዊ መብትን መጣስ ለመከላከልና መብቱን ለማስከበር እስከ ምን ድረስ መገለቅ አለበት? የሚለው መነሳት ያለበት ነው። የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ ማለት ይገባል።

በመጀመሪያ ደረጃ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች በጥንቃቄ ስንመለከት ህግ አውጪው ለህገ-መንግስታዊ ስርዓት በተለይም ደግሞ ለህግ የበላይነት ልዩ ትኩረት መስጠቱን እንረዳለን። ለዚህም ነው በምዕራፍ ሶስት ስር የተመለከቱት የመሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ወዲያው ሊፈፀሙ በሚችሉበት መንገድ እንጂ በምኞት ደረጃ ያለተገለፁት። እነዚህን መብቶች ፍርድ ቤቶች (እንደ ማንኛውም የመንግስት አካል) የማስፈፀም ግዴታ ተጥሎባቸዋል። በህገ- መንግስቱ የተቋቋሙት ፍርድ ቤቶች ደግሞ የሚመሩበት በመሰረቱ በዚህ እና በሌሎች ህጐች ነው። ስለሆነም የተከሳሽ የመከላከል መብት በእውቀት እና ገንዘብ ማነስ የተነሳ ሊጣስ ከሆነ ተከላካይ ጠበቃ በመመደብ ጉድለቱን ማስተካከል ከፍርድ ቤት ይጠበቃል ማለት ነው። የተከላካይ ጠበቃን መመደብ የማይቻል በሚሆንበት ጊዜም ፍርድ ቤት ይህን ክፍተት ለመሙላትና ሰብአዊ መብት እንዲከበር ለማድረግ በሚያስችለው ርቀት ገብቶ መካስ አለበት። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የህገ-መንግስቱ መንፈስ መመርመር ያስፈልጋል። ህገ-መንግስቱ በግልፅ ድንጋጌ እውቅና አይሰጣቸውም ተብለው የቆዩ የባህል ፍርድ ቤቶች አውቅና ማግኘታቸውንና ተደራጅተው እንደሚሰሩ ይደነግጋል። የባህል /የኃይማኖት/ ፍርድ ቤቶች እንደመደበኛው ፍርድ ቤት ፍትህን የሚያስተዳድሩት ህግን ሙያዊ በሆነ መንገድ በመተንተን ሳይሆን እውነት ላይ ለመድረስ በመጣር ብቻ ነው። እነዚህ ፍርድ ቤቶች እውነትን /truth/ ለማውጣት ቅርብ ናቸው ይባላል። ስለሆነም ከህገ-መንግስቱ ከዳኝነት ስርዓቱ በአጠቃላይ "እውነት" እና "ፍትህ" (Truth እና Justice) የሚገኝበት እንደሆነ ፍላጐት አለው ማለት ነው። እውነት ላይ ለመድረስ የሚያስችል የዳኝነነት ስርዓት የሚኖረው ደግሞ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ብቻ ውሳኔ የሚሰጥ ፍርድ ቤት

ሲኖረን ሳይሆን በመሀል በክርክር የሚዛቡና ሰብአዊ መብትን የሚነሱ አሰራሮችና ክርክሮች (አቀራረቦች) ካሉ ጣልቃ በመግባት የሚያስተካክል የዳኝነት ስርዓት ነው።

በዚህ ረገድ የስነ ስርዓት ህጋችንን ብንመለከት እንኳን የዳኝነት አካሉ በራሱ ተነሳሽነት ሊፈፅማቸው የሚገቡ (a pro-active Justice activities) ተግባራት በየቦታው እናገኛቸዋል። ለምሳሌ አንድ ተከሳሽ ለቀዳሚ ምርመራ ፍ/ቤት ሲቀርብ የቀረበበት አላማ የጥፋተኝነት ወይም የንፅህና ውሳኔ ላለመቀበል መሆኑን ፍ/ቤት እንዲነግረው ህጉ ያዛል። ለሚጠየቀው ጥያቄ መልስ መስጠት እንደማይገደድም ይነገረዋል። የሰብአዊ መብት ጥሰትን ሊያስከትል የሚችሉ ክሶች በአንድ ላይ ተጣምረው ከቀረቡ ክሶቹ እንዲነጣጠሉ ፍ/ቤት ማዘዝ አለበት። የግለሰብ ሰብአዊ መብትን የሚጥስ የክስ ቻርጅ የቀረበም እንደሆነ ተሻሽሎ እንዲቀርብና መብት በሚያስከብር መልኩ ክርክሩ እንዲቀጥል ማዘዝ አለበት።

አዲስ የወንጀል ክስ ሲቀርብ ክርክሩ መቀጠል ያለበት የክርክሩ መቀጠል የተከሳሽን የመከላከል መብት የማይጥስ መሆኑን ፍርድ ቤቱን ራሱ ከመረመረ እና ካረጋገጠ በኋላ ነው። በሌላ በኩል የክስ ቻርጅ የተቀበለ ፍርድ ቤት ክሱን ለተከሳሹ ብቻ በማንበብ አይወሰንም። እያንዳንዱን ክስ ለተከሳሹ በንባብ ማሰማት ብቻ ሳይሆን በሚገባ ማስረዳትም ይጠበቅበታል። የክሱን ይዘት የተረዳ ተከሳሽ ለክሱ መልስ ከመስጠት ይልቅ ዝምታን ሲመረጥ መብቱን የበለጠ የሚያስከብረው ማስረጃ ሲቀርብ በመሆኑ ፍርድ ቤት ማስረጃ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይገደዳል። በሌላ በኩል ተከሳሹ ያመነ ቢሆንም እንኳን ፍርድ ቤቱ "አስፈላጊ ሆኖ የሚገኘውም በግሀ-መንግስቱ የተረጋገጡ የተከሳሽ መብቶች በይበለጥ የሚከበሩት ክሱ በማስረጃ ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑን ፍርድ ቤቱ በማመን አንዲ ቀጠሮ በማራዘም በሌላ መልኩ የሰብአዊ መብት ጥሰት ለመፍጠር አይሆንም።"

ተከሳሽ በሰጠው የእምነት ቃል መነሻነት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠም በኋላ ክሱ በሚሰማበት ጊዜ የክህደት ቃል መመዝገብ እንዳለበት ፍ/ቤቱ ካመነ ይህንኑ በራሱ ተነሳሽነት በመመዝገብ የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ውድቅ እንዲያደርግ ህጉ ይፈቅዳል። የዐ/ሕግ ምስክሮች ቃል በሚሰማበት ጊዜም ፍ/ቤት ለቀረበው ምስክር ማንኛውንም አይነት ጥያቄ በማንኛውም ጊዜ ለመጠየቅ ይችላል። የዐ/ሕግ

ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ አስፈላጊ ከሆነ የተከሳሽ /የግለሰቡ/ ሊሰሙ ይችላሉ፡፡ ተከሳሹ ቃል ለመስጠት ከፈለገ መጀመሪያ ይሰጣል፡፡

ፍርድ ቤትም ነገሩን ለማብራራት የሚያስችል ጥያቄ ሊጠይቀው ይችላል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ፍርድ ቤቱ በማንኛውም ጊዜ ምስክር ተጣርቶ ቃል በመቀበል ይችላል፡፡ ከሳሽ ወይም ተከሳሹ ግለሰብ በማስረጃ ያቀረቧቸውን ምስክሮች እንዲሰሙላቸው መጠየቅ የሚችሉ ሆነው ፍርድ ቤት ለእነዚህ ተጨማሪ ምስክሮች መጥሪያ የሚልከተው"ለፍሬ ነገሩ አስፈላጊ" መሆናቸውን በመገንዘብ ነው፡፡ ተጨማሪ ዝርዝሮች በስነ-ስርአት ህጉ የትምህርት ፅሁፍ ውስጥ ይገኛል፡፡ እዚህ ጋር ለማሳየት የተፈለገው የዳኝነት አካሉ እንደማንኛውም የመንግስት አካል መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶችንና ነፃነቶችን የማስከበር ግዴታ ያለበት ከመሆኑ በተጨማሪም ይህንን ከግድ ኃላፊነት በመወጣት እንዲችል የስነ-ስርዓት ህጉ ምቹ መሆኑን ነው፡፡ የግለሰብ መብቶች እንዳይጣሱ ክክስ ማንበብ አንስቶ ፍርድ እስከ መስጠት ድረስ ለዳኝነት አካሉ በራሱ ተነሳሽነት ጣልቃ የሚገባባቸው መንገዶች በርካቶች ናቸው፡፡ ተከሳሹ የመስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ ባለመቻሉ የመከላከል መብቱ ይጠባል በተባለ ጊዜ የተከላካይ ጠበቃን ሚና በመያዝ መስቀለኛ ጥያቄ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ ጠቃሚ ማስረጃ በተከሳሹ እውቀት ማነስ ወይም ጉድለት ሳይቀርብ ሲቀር የመብት መጣስን የሚያስከትል እስከሆነ ድረስ ማስረጃው ቀርቦ ለፍርድ እንዲያገለግል ማድረግ አለበት፡፡ እውነትን ማውጣት እስከቻለ ድረስ በግራ ቀኙ የቃል ፣የፅሑፍ ክርክር እንዲሁም የማስረጃ አቀራረብ እና ምዘና ውስጥ በሰፊው እና በንቃት የዳኝነት አካሉ ሊሳተፍ ይገበዋል፡፡ ይህ የንቃተ ተሳትፎ (Judicial Activism) በማንኛውም ጊዜ መጠን የሚደረገው ግን ለስነ-ስርዓት ህጉ ድንጋጌዎች አገላለፅ "አስፈላጊ ሆኖ እስከተገኘ" ድረስ ብቻ ነው፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ የሚባለው ደግሞ ዳኝነት በነፃነት እና በገለልተኝነት መከናወን ያለበት መሆኑን በመጣስ ሳይሆን በህጉ መንግስቱ ላይ የተደነገገውን የመሰረታዊ መብቶችንና ነፃነቶችን የማስከበር ግዴታን ለመወጣት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አሁን የሚታየው ተከራካሪ ወገን ያልጠየቀው ጥያቄ ውስጥ ለመግባት ምን አገባኝ እምነት የህገ-መንግስቱን ሰብአዊ መብቶች ለማስከበር ከተጣለው ግዴታ አንፃር ቢቻል በእምነት መከበር ያለበት ነው፡፡ የዳኝነት አካሉ በሀገራችን ያለውን የባለሙያ እጥረት፣ የተከሳሽን ተከላካይ ጠበቃ የማቆም የገንዘብ አቅም፣ የከሳሽን በተሻለ መልኩ መደራጀት የህጉን ቴክኒካል ችግሮች

ተመልክተው "የጨዋታውን ሜዳ" ወጣ ገባነት በማለስለስ መብቶች (የግለሰብ መብቶች) መከበራቸውን በማረጋገጥ ሂደቱ ውስጥ ጣልቃ እየገቡ መቆጣጠር ይገባቸዋል፡፡ ይህ የህገ መንግስቱን ድንጋጌ ማስከበር ነው፡፡ ህግን አለማክበር ደግሞ የስነ-መግባር ተጠያቂነት የሚያስከትልና ከፍተኛ የሆነ የሙያ ብቃት እና ቅልጥፍና ማጣትን የሚያረጋግጥ በመሆኑ በስነ-ምግባር ደንቦች መሠረት ተጠያቂነት የሚያስከትል ነው፡፡ አዲስ መስመር ከፍ ሲል በተመለከተው መልኩ ዳኞች ተግባራቸውን ሰፋ ባለ ግንዛቤ ማከናወን አለባቸው ማለት ግን ዳኞች በሁሉም ጉዳዮች ላይ ዳኞች ናቸው ማለት እንዳልሆነ ይሰመርበት ይገባል፡፡ በየትኛውም ሀገር ቢሆን ሁሉም ግጭት መፍትሔ የሚያገኘው በፍርድ ቤት አይደለም፡፡ እንዲያውም አብዛኛው ችግር ከፍርድ ቤት ውጪ በሌሎች የፍትህ አካላት እና በግለሰቦች የሚፈታ ነው፡፡ በአሜሪካን ሀገር የፖለቲካ ደግማ ጥያቄ /Question of political doctrine /የሚያስነሱ ጉዳዮችን ፍርድ ቤቶች አይመለከቱም፡፡ በዚህ ዳግማ መሠረት (በተለይ) በከፍተኛ የፌዴራል መንግስት አካላት መሀከል ግጭት ሲነሳ ጉዳዩ ከፍርድ ቤት ውጪ እንዲታይ መደረጉ የተለመደ ነው፡፡ በአሜሪካን አገር ለምሳሌ በዚሁ ዳግማ መሰረት ዋና ዋና የሚባሉ የህገ መንግስት ጥያቄዎች (የመንግስት ቅርፅ ሪፐብሊካን መሆኑ የውጪ ግንኙነት ላይ ያለን ስልጣን በተመለከተ፤ ህገ መንግስቱ የሚሻሻልበትን መንገድ በተመለከተ ወዘተ) Non-Justiciable ተብለው ፍርድ ቤት የማይዳኙቸው ሆኖም የተወሰኑ ናቸው፡፡ የቅርብ ዕሁፎች የሚያሳዩት ፌዴራል ጉዳዮች Non- Justiciable እየሆኑ ነው፡፡ ተመሳሳይ ጥያቄ በፖለቲካው ሂደት የሚፈታ ነው፡፡ በፈረንሳይም ከሞላ ጎደሎ ተመሳሳይ ነው፡፡ በእኛም በጀርመን አገር እነዚህ ጉዳዮች በህገ መንግስት ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ቢሆኑም አቅራቢዎች የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ብቻ የሚያቀርቧቸው ናቸው ተብለው በከፍተኛ ደረጃ ይተቻሉ፡፡ ለኛም ሀገር እኚ መጀመሪያውን አይነት ጥያቄ ተቀብሎ የሚያስተናግድ የፌዴሬሽን ምክር ቤት እና በፍርድ የውሳኔ ሰጪ አካላት አሉን፡፡ የዳኝነት አካሉ በፍርድ የሚወሰን ጉዳይ ላይ ሁልጊዜ የሚገኝ /Omnipotent/ እና መወሰን የሚችል / Omnipresent / ተደርጐ መወሰድ የለበትም፡፡ ዳኞች በአንድ ጉዳይ ላይ ፍርድ ከመስጠታቸው በፊት ጉዳዩ በዳኝነት እንዲቀርብ /Justiciable/ በግልፅ ህግ የተደነገገ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ጉዳዩ ለፍርድ ቤት የማይቀርብ / non Justiciable/ በሌላ አካል የፍርድ ስልጣን ስር ሆኖ ጉዳዩን የተመለከቱ እንደሆነ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ላይ የተመለከተውን ፍትህ የማግኘት ሰብአዊ መብት መሸረሸራቸውን

መገንዘብ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ አልፎ አልፎ የሚታይ ቢሆንም አንድን የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በክርክር የቤተክርስቲያን አስተዳደር አድርጐ ማስቀመጥ /መወሰን/ የሰራተኛን ሰብአዊ መብት ማስከበር ነው ወይስ የሰዎች ፍትህ የማግኘት መብት ማጥበብ? ለሚለው ሰልጣኙ ቢወያይበት የተሻ ነው፡፡ ለመግለፅ የተፈለገው የዳኝነት ስልጣን በግልፅ ህግ የሚሰጥ አንድ በእንደመታ (Implication) የማይሰጥ መሆኑን መገንዘብ ይገባል በማለት ነው፡፡

የህገ መንግስት በመተርጎም ረገድ የኢትዮጵያ ህገ መንግስት አቋም

መግቢያ

ባለፉት ሁለት አስርተ አመታት ህገ መንግስትን የመተርጎም ጥያቄ ከፍተኛ ትኩረት እያገኘ የመጣ ጉዳይ ሆኖል። ህገ መንግስትን ማን ይተረጎመው? ተርጓሚው እንዴት ይዋቀራል? ምን ዓይነት ስነ ስርዓት ይከተላል? የሚሉትን ጥያቄዎች አገሮች የየራሳቸውን የታሪክ፣ የባህል፣ የፖለቲካ እና የፍልስፍና ሁኔታዎች ግምት ውስጥ አያስገቡ ይወሰናሉ። በዚህ መሰረት የየአገሩ ልምድ የተለያዩ ቢሆንም በጥቅሉ የሚከተሉትን ሞዴሎች ይከተላሉ ለማለት ይቻላል። እንደ አማሪካ፣ ካናዳ፣ ጃፖን ፣ ግሪክ እና የመሳሰሉት አገራት ህገ መንግስትን የመተርጎምም ሆነ ሌሎች ህጐች ሁሉ ህገ መንግስቱን የማይቃረኑ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች ይሰጣሉ። የአስፈፃሚው አካል ውሳኔ ህገ መንግስታዊ አይደለም በማለት ውድቅ ማድረግ ይችላሉ። ይግባኝ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት (በአሜሪካ) የሚቀርብ ቢሆንም ጉዳዩ ላይ ጥቅም (መብት) ያላቸው ተከራካሪ ወገኖች ብቻ እንዲቀርቡ ይጠበቃል። የአስፈፃሚውንና የህግ አውጪውን ተግባር በዳኝነት ቁጥጥር (Subordination) ስር ማድረግ ያስፈልጋል በሚለው በተለመደው አስተሳሰብ መሰረት የመጣ ሞዴል ነው። ሁሉም የህግ መንግስት ጥያቄ ለመደበኛው ፍርድ ቤት የሚቀርብ ቢሆንም በይዘቱ ግን በአገሮቹ መካከል ልዩነት አለ። አንዳንዶች ይህንን ስልጣን በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ሲሆን (አሜሪካ) አንዳንዶች ደግሞ ለከፍተኛ ወይም ለጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚሰጡ ናቸው (ምሳሌ ህንድ)። በሌላ በኩል በጉዳዩ ላይ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ብቻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚያደርጉም አሉ (ምሳሌ አየርላንድ)።

በሌላ በኩል የተማከለ ልሬት ተፅዕኖ ያሳደረባቸው የአውሮፖ አገራት የህገ መንግስትን ትርጉም ከመደበኛው ፍርድ ቤት ውጪ ለዚሁ ተግባር በተቋቋመ "የህገ መንግስት ፍርድ ቤት" (Constitutional Court) ይሰጣሉ። ጀርመን አይነተኛ ምሳሌ

ናት፡፡ ይህ ፍርድ ቤት በመደበኛ ፍርድ ቤት በተለየ መልኩ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ህገ መንግስታዊ ጉዳዮችን በጭብጥነት ይዞ የሚመረምር ልዩ ፍርድ ቤት ነው፡፡ እንደ መጀመሪያው የፍርድ አይነት ቤት ስነ ስርዓት ሳይሆን ልዩ ስነ ስርዓትን የሚከተል ነው፡፡ መደበኛ ወይም ሌሎች ፍርድ ቤቶች የህገ መንግስት ጥያቄ (ትርጉም) ሲገጥሟቸው ይሔው ፍርድ ቤት መመሪያ እንዲሰጥበት ጉዳዩን የሚልኩትም ነው፡፡ ዳኞች ለተወሰነው ጊዜ በተለያዩ አካላት ሲመረጡ፤ የጀርመኑን ብንመለከት ይህ ልዩ ፍርድ ቤት ለ12 ዓመታት የሚያገለግሉ 16 ዳኞችን ሁለት ምክር ቤቶች (Bunds rat) እና (Bond stag) የሚሾሟቸው ናቸው፡፡ የልዩ ፍርድ ቤቱ መሰረቱም ያለፈው ኢ-ፍትሐዊ የአገዛዝ ዘመን (‘unjust regime) ተመልሶ እንዳይመጣ ህገ መንግስቱን (በጀርመን Basic Law) ለማስጠበቅ ነው፡፡

ሌላው ከመጀመሪያው ሞዴል ጋር የሚቀራረበው የስዊዝ ሞዴል ነው፡፡ በዚህ ሞዴል በፌዴራሉ ፍርድ ቤት ውስጥ ልዩ ፍርድ ቤት ያለና የትርጉሙን ጥያቄ "በፖ'ናል" የሚመልስ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ስልጣኑ ክፍለ ሀገራት (Cantons) የሚያወጧቸው ህጐች ከፌዴራል ህጐች ጋር መጣጣማቸውን መመርመር ብቻ ነው፡፡ የፌዴራል መንግስቱ ህጐች ህገ መንግስታዊ ለመሆናቸው የመመርመር ስልጣን የለውም፡፡

የኢትዮጵያ አቋም

ከፍ ሲል ከተመለከትናቸው ጥቅል ሞዴሎች የኢትዮጵያው አቋም የተለየ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ልዩነቶች የሚነሱት ከየአገሩ የግል ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት በመሆኑ የእያንዳንዱ አገር በራሱ የተለየ እንደመሆኑ መጠን የኢትዮጵያ ሞዴል ራሱን የቻለ መሆኑ የሚገርም አይሆንም፡፡ በአገራችን ህገ መንግስትን የመተርጐም ስልጣን የተሰጠው ለፌዴሽን ምክር ቤት ነው፡፡ ህገ መንግስቱን የኢትዮጵያ ህዝቦች ብሔር እና ብሔረሰቦች ተስማምተው ሲያወጡት የህግ ጉዳቶችን የተመለከቱ ከመሆናቸው በተጨማሪ የተበላሸውን የታሪክ፣ ባህል፣ ፖለቲካ፣ ማህበራዊ ግንኙነት በአዲስ መልክ ለማደስ መስማማታቸውን በሌላ ፅሁፍ ተመልክተናል፡፡ ስለሆነም የህገ መንግስቱ ጉዳይ የህግ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ከህግ በላይ የሆኑ ጉዳዮችን የያዘ ነው፡፡ ይህንን ጠንቅቀው

የሚያውቁት ህግ አውጪዎች ህገ መንግስቱን መተርጎም ቢያስፈልግ ራሳቸው ሊሚወክሉት ነገር ግን በታዋቂ የህግ ባለሙያዎች በሚታገዝ የፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተረጉም ማድረጋቸው ተገቢ ይመስላል። በዚህ ጉዳይ ላይ የህገ መንግስት ኮሚሽን ፀሐፊ ባደረጉት ንግግር በህዝቦች የፀደቀ ህግ ለህዝብ በቀጥታ ባልተመረጡ ባለሙያዎች ሊተረጉም አለመቻሉ፤ ይህ መሆኑ የዲሞክራሲውን ሂደት መግታት እንደሚሆን፣ ህገ መንግስቱ የህዝቦች የፖለቲካ ሰነድ (ውል) በመሆኑ በተዋዋዮቹ ብቻ መተርጎም ያለበት መሆኑን መግለፃቸው ይሰመርበታል። የህገ መንግስቱን አንቀፅ 8፣ 61 ስንመለከት የስልጣኑ ባለቤት የተመረጠው በአግባቡ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ መሆኑን እንረዳለን። በዚህ መሰረት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 62(1) ላይ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የህገ መንግስት የመተርጎም ስልጣን ተሰጥቷታል። በሌላ በኩልም በአንቀፅ 83(1) የፌዴሬሽን ምክር ቤት ህገ መንግስታዊ ክርክር ሲነሳ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ተሰጥቶታል። አንቀፅ 83(1) ርዕሱ ህገ መንግስትን ስለመተርጎም የሚል ቢሆንም ይዘቱ ግን ክርክር ላይ ያተኮረ ነው። የህገ መንግስት ትርጉም ጉዳይ የተከራካሪ ወገን ባለበት ጊዜም ሊነሳ ስለሚችል ሁለቱ "Constitutional Interpretation constitutional dispute" እኩል ናቸው ተብሎ የሚወሰዱ አይመስሉም። ክርክር ባልተነሳበት ጊዜ ህገ መንግስቱን መተርጎም 'Abstract Review' ሊባል የሚችል ሆኖ አንድን ጉዳይ (ክርክር) በመጥቀስ የሚፈፀም አይሆንም። Objective Review ተብሎም ይጣራል። በአገራችን የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ እንድ መጀመሪያው የአሜሪካ ሞዴል በክርክር መነሻነት ብቻ ምላሽ የሚያገኝ ጥያቄ አለመሆኑን ድንጋጌዎች ያስረዱናል። የህግ አውጪው ቃለ ጉባዔም በዚህ ጉዳይ ላይ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚያደራጀው የህገ መንግስት አጣሪ ምን ስልጣን ይኖሩታል በሚለው ላይ ባደረገው ውይይት "ህገ መንግስት ቅራኔ ክርክር ሲቀርብለት እንደሚመለከትና እንዚህን ክርክሮች ደግሞ ፍርድ ቤት ወይም በባለጉዳዮች ሊቀርቡ እንደሚችሉ" ጠቁሞ "ህገ መንግስት አተረጓጎምን በሚመለከት የሚነሱ ጉዳዮችን" ጨምሮ እንደሚያይ ገልፆል።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት የህገ መንግስት ትርጉም ለመስጠት ስልጣን ያለው ሲሆን የሌሎች የፍትህ አካላት ስልጣን ምንድን ነው? የትርጉሙ ውጤትስ ምንድን ነው? የሚሉትን ማንሳት ተገቢ ነው።

በህገ መንግስቱ ላይ እንደተመለከተው የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ሁለት ወሰኖች አሉት

1. ህገ መንግስቱን በራሱ መተርጎም ሲያስፈልግ
2. በህግ አውጪው የወጡ ህጎችን ህገ መንግስታዊነት ለማረጋገጥ በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ በትርጉም መወሰን ሲያሰፈልጉ ናቸው።

የመጀመሪያው በአንቀፅ 61 ላይ የተመለከተ ሲሆን ሁለተኛው በአንቀፅ 84 ስር የተመለከተ ነው።

የመጀመሪያውን ነጥብ አስመልክቶ የህገ መንግስቱን ድንጋጌ ስንመለከት አቀራረፁ በዚህ ነጥብ ላይ ብቸኛ ውሳኔ ሰጭ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው ለማለት አይመስልም። የመሰረታዊ ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶችን የማስፈፀም ግዴታ ሌሎች የፍትህ አካላትም (ፍርድ ቤት) አለባቸው። ህገ መንግስቱን ለማስፈፀም ደግሞ መተርጎም ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ ማንም ሰው ኢ-ሰብአዊ ከሆነ አያያዝ ወይም ጥቃት መጠበቅ አለበት የሚለውን ድንጋጌ መፈፀም ቢያስፈልግ "ግርፋት" ኢ-ሰብአዊ ቅጣት ነው ወይንስ አይደለም? የሚለውን ለመመለስ ፍርድ ቤቶች ህጉን /ቃሉን/ መተርጎም ይኖርባቸዋል። ጭካኔ ምን ማለት ነው? የሚለው ጥያቄ ውስጥ ቢገባ ፍርድ ቤቶች በያዙት ጉዳይ ላይ ተርጉመው ውሳኔ መስጠት ያለባቸው ይመስላል። ማንኛውም የፍትህ አካል የሚሰጠው ውሳኔ ከህገ መንግስቱ ጋር የማይጣጣም ከሆነ ተፈፃሚነት ስለማይኖረው የሚሰጧቸው ውሳኔዎች ሁሉ ህገ መንግስቱን በመመርመርና በመተርጎም መሆን አለበት (አንቀፅ 9)። አንድ ሰው በቀረበበት የወንጀል ክስ ከዚህ በፊት የተቀጣበት በመሆኑ በድጋሚ ሊከሰስ አይገባውም በማለት ዐ/ህግ፣ ፖሊስ ወይም ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቢሰጥ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 23 ላይ የተመለከተውን "የመጨረሻ ውሳኔ" "ጥፋተኝነት" ፣ "በነፃ መለቀቅ" ወዘተ የሚሉትን ግምት ውስጥ በማስገባት እና በመተርጎም ነው""

በተወካዮች ምክር ቤት የፀደቀው የህገ መንግስቱ ረቂቅ አጭር ማበራሪያም የዳኝነተ አካሉ በህገ መንግስቱ ምዕራፍ 3 ስር የተመለከቱትን የሰበአዊ መብቶችና

ነባነቶችን ድንጋጌ መተርጎም እንደሚችሉ ይጠቅሣል፡፡ የዳኝነት አካሉ በዚህ ጉዳይ ላይ ትርጉም እንዳይሰጥ በግልፅ ባለመከልከሉም ይመስላል አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 3 ስር ህገ መንግስቱን በሚመለከት የሚነሱ ጉዳዮች ላይ የፌዴራሉ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል ተብሎ የተደነገገው፡፡ ይህ ማለት ግን የህገ መንግስት ጥያቄ ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ሁሉ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ለህገ መንግስት አጣሪ ጉባዔ ሳይመሩ ውሳኔ ይሰጣሉ ማለትም አይደለም፡፡

የዳኝነት አካሉ ይህን መሰል ጥያቄዎች ለአጣሪው ጉባዔ መላክ የሚገባው ከሚሆንባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ “በፌዴራል መንግስትም ሆነ በክልል መንግስት ህግ አውጪ አካላት የሚወጡ ህጐች” ከህገ መንግስቱ ጋር ይጋጫሉ የሚል ጥያቄ ወይም ክርክር ሲቀርብለት ነው፡፡ ይህ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 84(1) ላይ የተደነገገ ሲሆን በዚህን ጊዜም ቢሆን የዳኝነት አካሉ የህገ መንግስት ትርጉም ሊፈፅም የሚችልባቸውን ነጥቦች ይጠቁመናል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የመጣው ህግ ሁሉ ከህገ መንግስት ጋር ይጋጫል የሚል ክርክር ሲነሳ ፍርድ ቤቶች በደፈናው ጉዳዩን ለአጣሪው ይልካሉ ማለት ያስቸግራል፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ አረንጋዴ፣ ቢጫና ቀይ ነው ከሚለው ጋር ያጋጫል የሚል ክርክር ቢነሳ ጥያቄው በእርግጥ መሠረት ያለው ለመሆኑ በፍርድ ቤት መጣራት ያለበት ይመስላል፡፡ ይህ ጥያቄ ሳይጣራ ለአጣሪው ቢላክ የህገ መንግስቱን መንፈስ የተከተለ የፍርድ ቤት ኃላፊነትንም ያገናዘበ አይመስልም፡፡ ስለሆነም በገለፅነው ምሳሌ አይነት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ፍርድ ቤቶች የቀዳሚ ህገ መንግስታዊ የትርጉም ስራ ይሰራል ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል በፌዴራሽን ምክር ቤት የተሰጠው ስልጣን በፌዴራል እና በክልል ህግ አውጪ አካላት የወጡ ህጐች ከህገ መንግስቱ ጋር ይጋጫሉ የሚል ጥያቄ በተነሳ ጊዜ ነው፡፡ በአገራችን የህግ ተዋረድ ህግ የምንላቸው በህግ አውጪውም ሆነ አስፈፃሚው ወይም ሌላ ህግ በማውጣት ስልጣን በተሰጠው አካል በነጋሪት ጋዜጣ (ክልላዊ ጋዜጣ) ታትመው የወጡትን ህጐች ሁሉ ነው፡፡ (ህግ ማለት በአስፈፃሚው የወጡ ህጐች/ ትዕዛዞች ፣ ደንቦች መመሪያዎች ማስታወቂያዎች ወዘተ ጭምር ነው)፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 9 ላይ በግልፅ እንደ ተደነገገው ከህግ አውጪው ውጪ ያሉ ማንኛውም የፍትህ አካላት ማንኛውም ህግ ወይም የመንግስት አካል (ባለስልጣን) ውሳኔ

ከህገ መንግስቱ ጋር የማይጋጭ እስከሆነ ድረስ የማስፈፀም ግዴታ አለበት፡፡ እነዚህ ሁሉ ህጐች ውሳኔዎች ከህገ መንግስቱ ጋር የሚጋጩ በመሆናቸው ተፈፃሚ ሊሆኑ አይገባም የሚል ክርክር በሚነሳ ጊዜ የፍትህ አካሉ ትርጉም የመስጠት ስልጣን ይኖረዋል፡፡ በእርግጥ ከህገ መነግስቱ የምንረዳው ይህ ስልጣን የዳኝነት አካሉ ያለው መሆኑን ሲሆን አዋጅ ቁጥር 250/93 በአንቀፅ 17(2) ላይ የህገ መንግስት አዳረ ጉባዔ "ማንኛውም ህግ የመንግስት አካላት ወይም የባለስልጣን ውሳኔ ስለ ህገ-መንግስቱ ጋር ይጋጫል የሚል ጥያቄ ሲቀርብለት መርምሮ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴራሽን ምክር ቤት እንደሚያቀርብ ይደነግጋል፡፡ ለፌዴራሽን ምክር ቤት እንደሚያቀርብ ይደነግጋል፡፡ ይህ ስልጣን በህገ መንግስቱ ለአጣሪ ጉባኤ /ለፌዴሬሽን ምክር ቤት/ ከተሰጠው ስልጣን የሰፋ ስለሚመስል አንቀፁ ከህገ-መንግስቱ አንቀፅ 34/2/ጋር ይገጫል ወይስ ይጣጣማል ? የሚለው ጥያቄ በራሱ በምክር ቤቱ የሚወሰን ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተያዘው ጉዳይ ላይ አሁንም ብቸኛ (Sole and Exclu) ስልጣን ያለው አጣሪ ጉባኤ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ የሚደርስ አይመስልም፡፡ በእርግጥ በመሰል ጉዳቶች ላይ ለአጣሪው ጉባኤ የሰጣቸው ውሳኔዎች ይህንኑ የማደግፉ ናቸው፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ ሰልጣኞች ይወያዩበት፡፡

የትርጉም ውጤት

በመግቢያችን ላይ የተመለከትናቸው የተለያዩ ሙህሮች ለህገ መንግስት ትርጉም የተለያየ ውጤት ይሰጡታል፡፡ በአሜሪካን ሀገር በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤቱ የተሰጠ የህገ-መንግስት ትርጉም ለሁሉም አካላት አስገዳጅ ነው፡፡ በጀርመን የተመለከትን እንደሆነም የህገ-መንግስት ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የህግ ክፍል ያለው ነው፡፡

ወደ ሀገራችን ስንመለስ በፌዴሬሽን ምክር ቤት የተሰጠ የህግ ትርጉም ውጤቱ ምን እንደሚሆን በአ.ቁ. 259/93 አንቀፅ 11 ላይ ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሰረት የተሰጠ ውሳኔ ለዚሁ ተግባር በሚዘጋጀው ልዩ መጽሔት መውጣት ያለበት ሲሆን ውሳኔው በሚነሱ ተመሳሳይ ጉዳዩች ላይ አስተገዳጅነት ባህሪ አለው፡፡ ስለሆነም በፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚሰጡ የህገ መንግስት ትርጉም ውሳኔዎች በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በሁሉም ሹሞች/አካላት/ ላይ ተፈፃሚ ናቸው፡፡ በህግ አውጪው ከወጡት ህጐች የበላይ

ነገር ግን ከህገ -መንግስት ስር የሆነ የህግ ውጤት ያለው ውሳኔ ነው ለማለትም ይቻላል። ስለሆነም ህገ መንግስታዊ አይደለም የተባለ የህግ አውጪው ድንጋጌ ወይም ህጐች ተፈፃሚ አይሆኑም ማለት ነው። የፌዴሬሽን ምክር ቤት ይህ ውሳኔ ወደ ኋላ (Retroactively) ተመልሶ እንዲያገለግል ካልወሰነ በስተቀርም ውሳኔው ውጤት የሚኖረው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ወደፊት ነው።

በሌላ በኩል ቀሪ የፍትህ አካላት በተለይ የዳኝነት አካሉ ከላይ በተመለከተው አግባብ የሚሰጠው የህገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ ውጤት የሚኖረው በቀረቡበት ተከራካሪ ወገኖች ላይ እና በተያዘው ጉዳይ ላይ ብቻ ነው። ይሁንም እንጂ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር ስልጣኑ ሰብአዊ መብቶች በተመሳሳይ መልኩ የሚሰጡ ውሳኔዎች ባለጉደዮች በሁሉም ፍርድ ቤቶች ዘንድ አስገዳጅ መሆኑን መዘንጋት አያስፈልግም።

የአተረጓጐም ንድፈ ሀሳብ (theories Canons of Interpretation)

የፌዴሬሽን ምክር ቤት እና ቀሪ የፍትህ አካል /በተለይ ሰብአዊ መብትን ለማስከበር/የህገ-መንግስት ትርጉም ይሰጣል፡ ስንል ህጉን እንዴትና በምን መንገድ ሊተርጉሙ ይችላሉ/ይገባል/ የሚለው ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። ህገ-መንግስቱን ለመተርጐም የተለያዩ የህግ ጐራዎች የተለያዩ መንግዶችን ይጠቀማሉ። በአብዛኛው የተለመደውን የሌሎች የቀረ ህጐች አተረጓጐም ንድፈ ሀሳብ መከተል ሲሆኑ ህገ-መንግስት የበላይ እና የተለየ ህግ እስከሆነም ድረስ ተጨማሪ የአተረጓጐም ንድፈ ሀሳቦች ይኖራሉ። እነዚህን በጥቅሉ እንደሚከተለው እናያቸዋለን።

1. *Literal theory (ቃላት ፣ቋንቋ)*

ይህ የአተረጓጐም ንድፈ ሃሳብ ቀደም ሲል ወሳኝ የነበረ ነው። አሁን የሚወጡ ህጐች ውስብስብ ሃሳብን የያዘ ይሁን እንጂ በተቻለ መጠን ውስብስብ ሃሳብ በቀላል እና ለሁሉም ሰው በሚገባ ቋንቋ የሚገለፁበት ናቸው። ቃላት ተራ /የመዝገብ ቃላት/ ትርጉማቸውን ይዘው እንደገቡ ይፈለጋል። ይሁን እንጂ ቃላት ከቃላት ወጥተው የህገ-መንግስቱ ቃል በሚሆኑበት ጊዜ ተራ ትርጉም አይሰጣቸውም። "ሁሉም ሰው

በህይወት የመኖር መብት" አለው የሚለው የሰብአዊ መብት ድንጋጌ ስድስት ቃላት ያሉት ነገር ግን ለሰው ልጅ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን መብት የያዘ ነው። "ህይወት ምንድ ነው ? የሚለውን ግን ተራው የቃሉ ትርጉሙ አይመልሰውም። ስለሆነም በህገ መንግስቱ ውስጥ /በተለይ ሰብአዊ መብትን አስመልክቶ/ የፍትህ አካላት የቃለት ትርጉም ሲገጥማቸው ተራው የቃላት ትርጉም አንድ የትርጉም አማራጭ ሆኖ ወደ ህጉ "ህጋዊ ትርጉም "ሊያድግ የሚችል መሆኑን መረዳት ይገባል። ቃላት የህግ አውጪውን ሃሳብ፣ምኞት ፣መነሻ በግልፅ እስካስቀመጡልን ድረስ "ፍትሃዊ" ናቸው። ይህ እስካለሆነ ድረስ የፍትህን ቋንቋ (Justice of language)ሳይሆን language of Justice መፈለግ ግድ ነው። ይህን ማድረግ ሲቻል ተመሳሳይ ቃላት ከህገ-መንግስቱ በፊት በነበረው ህገ-መንግስት ውስጥ ቢኖርም የተለየ ትርጉም ሊሰጠው ይችላል። ዝርዝር በውይይት ይዳብራል።

2. <u>የህግ አውጪ ሃሳብ ንድፈ ሐሳብ (Intention theory)</u>

የህግ አውጪው ሃሳብ አግባብ ባለው ቃል ላይገልፅ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ ሃሳቡ ከቃሉ ጋር ሊጋጭ ይችላል። በዚህ ጊዜ በህገ-መንግስቱ እና ከህገ-መንግስቱ ውጪ በመጀመሪያ የህገ-መንግስቱን አጠቃላይ ይዘት(Content) መመልከት ተገቢ ነው። ህገ-መንግስቱ ከመነሻ እስከ መድረሻው ወጥ በሆነ ሎጂክ ተያይዟል ብሎ ማሰብ ይገባል። ይህ Systematic ወይም Logical interpretation ይባላል። ይህ የሚታለፍ ቢሆን ከህገ መንግስቱ ውጪ ያሉ ሌሎች ሰነዶችን መመርመር ያስፈልጋል። "Macro-text" ሊባሉ ይችላሉ። የህግ ስርዓቱ& የፖለቲካ እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱ ፣አለም አቀፍ የህግ ስርዓት፣ሀገር ውስጥ ሀገራችን የምትመራበት ልዩ ልዩ የፖሊስ ሰነዶች ወዘተ ሊካተቱ ይችላሉ። የሲስተማቲክ ትርጉም ዋናው ስራ ሰነዱን ከእነዚህ ሰነዶች ጋር ማስተሳሰር ነው። ያሉትን ሀብቶች መጠቀም ይገባል። ለምሳሌ የህገ-መንግስት አርቃቂም የሰብአዊ መብት ትችት፣ የህግ አውጪው አባላት በፅሁፍ ወይም በቃል የሰጡት አስተያየት ከህገ-መንግስት ሰብአዊ መብት ድንጋጌ ባሻገር የነበሩ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች እና በሰብአዊ መብት ሀገሪቱ ያሉት ታሪክ መመልከት ተገቢ ነው። ስለሆነም ህገ-መንግስት ተርጓሚው በተለይ በምዕራፍ ሶስት ለተቀመጠው የመሰረታዊ መብት እና ነፃነት ድንጋጌ በቀላሉ የማይሻሻል በመሆኑ ህጉ አላማውን እያሳካ ሀያው ያለው (Dynamic) እንደሆነ ያለፈውን ታሪክ አዲሱን ፣የቴክኖሎጂ

፣ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እውነታ እያጣጣሙ መመርመር ይኖርበታል። በህግ አውጪው ወይም በአርቃቂው ውይይት ጊዜ በርካታ ለተለያዩ ሐሳባች ሊነሱ የሚችሉ በመሆናቸው የህግ ፣ አውጪው ሃሳብ ሲፈለግ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በእርግጥ ያሰቡት የትኛውን ነው የሚለውን መለየት ያስፈልጋል። ሁል ጊዜ የበላይ የሚሆነው ህገ-መንግስቱ የፈቀደው ብቻ መሆኑን መዘንጋት የለበትም።

3. Teleological Interpretation (ግብን መሰረት ያደረገ አተረጓጎም)

ይህ የአተረጓጎም መንገድ ተርጓሚው/የፍትህ አካሉ/ የህጉን መንፈስ እንዲፈለግ የሚያደርግ ነው። ከሌሎች የሚለየው ህግ ተርጓሚው ፍትህን ፣እና የህብረተሰቡን እሴቶች ግምት ውስጥ እንዲያስገባ የሚጠይቁ መሆኑ ነው። እንደ ነፃነት፣እኩልነት፣ፍትሐዊነት፣ due process ለመሳሰሉት መርሆዎች /እሴቶች/ ዋጋ መስጠትን ይጠይቃል። የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች በተለይ በዚህ መልክ ላይ ተደርገው መተርጎም ያለባቸው እንጂ እንደሌሎች ህጐች ጥብቅ ሆነው (Legalistically) መተርጎም ያለባቸው አይደሉም።

4. ንፅፅራዊ ንድፈ ሀሳብ (comparation theory)

ይህ ንድፈ ሀሳብ የተፃፈ ህግ ባላቸው ሀገሮች መተግበሩ ጠቃሚ ነው። የአንድ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ አላማው በሌላ ተመሳሳይ ድንጋጌ ውስጥ ሊገኝና ሊገለፅ ይችላል። በተለይ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች አለም አቀፍ ይዘት ያላቸው በመሆኑ ይህ ንፅፅራዊ ትርጉም ጠቃሚ ነው። ለሀገራችን ይህ ከህጉ መንግስት አንቀፅ 9/4/ እና 13/1/ አንፃር ጠቃሚ ነው።

የህገ መንግስት አተረጓጎም መርሆዎች

ሀገራችን የህገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄን ማስተናገድ የጀመረችው በቅርብ ጊዜ ወዲህ መሆኑና ተግባሩን በተግባር ያልዳበረ በመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ በተለይ የሀገራችን መርህ ነው ለማለት የሚቻል መርህ ማግኘት ያስቸግራል። ይሁን እንጂ የትርጉም ስራ ለመስራት በአ.ሰ.251 መሠረት፤

1. በተለይ የሰብአዊ መብትንና ነፃነትን የሚመለከት ትርጉም ሲኖር ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት የሚመሩባቸው መርሆዎች ለትርጉም በቀጥታ ተፈፃሚ ናቸው፡፡
2. ለትርጉም ጠቃሚ ናቸው የሚባሉ ሌሎች መርሆዎችንም የፌዴሬሽን ምክር ቤት እና ተርጓሚው ለይቶ ስራ ላይ መዋል ይችላል፡፡

ስለሆነም በሌሎች ሀገሮች ልምዶች በጥቅሉ የሚከተሉት መሆናቸውን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

- የህገ መንግስታዊ ጭብጥ አግባብነት፤ በተነሳው ህገ-መንግስታዊ ጥያቄ ላይ ምላሽ ለመስጠት በስፋት እና ጠቅላላ የትምህርት አይነት ውይይት ውስጥ ከመግባት ጭብጡን ብቻ ለይቶ መመርመር ያስፈልጋል (Reference of constitutional issue)
- ***<u>የህገ መንግስታዊነት ግምት</u>*** ፡- የወጣ ህግ ህገ-መንግስታዊ ነው የሚል መነሻ መያዝና ክርክር /ወይም ጥያቄ/ የሚያቀርበው ወገን በተቃራኒው ኢ-ህገ-መንግስታዊ ነው የሚለውን እንዲያስረዳ ማድረግ (Presumption of constitution ality)
- ***<u>ነጣጥሎ መመልከት</u>***፡- የአንድ አዋጅ የተወሰነ ድንጋጌ ብቻ ኢ-ህገ መንግስታዊ ከሆነ አዋጅ በአጠቃላይ ላይሸር ይችላል (Doctrine of Severability)
- ***<u>ብዙ ትርጉምች</u>***፡- አዋጁ& ህጉ በርካታ ትርጉመ የያዘ ከሆነ አዋጁን ሊያፀናውና ከህገ-መንግስቱ ጋር የሚጣጣመውን ትርጉም እንዲመረጥ ማድረግ (Principle of conformity)
- ***<u>የህገ-መንግስት የበላይነት</u>*** ፡- የትኛውም መንገድ /ንድፈ ሀሳብ/ቢመረጥ የህገ-መንግስቱን እንጂ ሌላውን መንገድ የበላይ የሚያደርግ አይመርጥም (Supermacy of Constitution)
- ***<u>ተመጣጣኝ</u>***፡- የህገ-መንግስት ትርጉም ሲሰጥ የሰብአዊ መብት ገደብ የሚያስከትል ከሆነ ጉዳዩ ሊጠብቀው እስከሚገባው እሴት ሰብአዊ መብት ድረስ ብቻ ተወስዶ መተርጉም አለበት (Principle of paportiondith)
- ***<u>የህገ-መንግስት አንድነት</u>***፡- የህገ መንግስት ጠቅላላ ድንጋጌ አንድ ራዕይ፣ እሴት እና ውጤት አለው ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ ሁሉም አይነት የጋብቻ መብቶች

ተመሳሳይ ውጤት እና ግብ አላቸው ብሎ እንደማሰብ ነው። (unit of the constitution)

ከዚህ ውጪ እንደ Principles of legislation policy and motives, the pith and substance test, problem of evidence እና ሌሎች መርሆዎች በውይይት ይዳብራሉ።

የህግ ተርጓሚው አካል በተለይ የሰብአዊ እና መብቶችና ነፃነቶችን ድንጋጌ በሚተረጉምበት ጊዜ ከላይ ለተዘረዘሩትን ንድፈ ሀሳቦች እና መርሆዎች በተናጠል ወይመ በጣምራ/ተመራጭ/ሊጠቀምባቸውና የህገ-መንግስቱንና የሀገራችንን ራዕይ በሚያሳካ መልኩ ህይወት ሊሰጠው ይችላል።